Dmujids Volume 7 Issue I 2023 DOI: 10.20372/dmujids 1000

# የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሰዋስው እውቀትና የሚታዩባቸው ዋና ዋና ሰዋስዋዊ ስህተቶች ፍተሻ (በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርት ቤት ተተኳሪነት)

*አለማየሁ ተመስገን*[1]

**በደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቋንቋ (ዎች) እና ሥነጽሑፍ -አማርኛ ትምህርት ክፍል**

Corresponding E-mail: alemayehu_temesgen@dmu.edu.et

**Abstract**

*For Many years, in Language teaching, Grammar had a big role. It was assumed that Language teaching is Grammar teaching. Even now adays, Grammar plays a big role. Taking this in to consideration, the main objective of this study was to evaluate the grammar (language accuracy) knowledge and main grammatical errors of teachers who teach Amharic in grade levels from grade 9 to 12. Five Secondary Schools were selected by using Convince Sampling method. From these Schools, 46 teachers were selected by using Comprehensive sampling technique. Then, the data was gathered through a grammar test provided for teachers. The test is consisted of 35 multiple choice items which focus on the different grammar aspects of Amharic. Data was analyzed through a One Sample T-test analysis technique and error count method. Taken the analysis made through the data for granted, the finding shows that the teachers' grammar knowledge is labeled as poor (N= 46, t= -4.69) = 29.8, P< 0.05). For the second objective, main grammatical error, Parallelism, flow of ideas, person and time, gender and number were ranked from first to last accordingly. Thus, the study has been concluded with some recommended tips like; teachers the case in point could enhance their grammar knowledge through reading various grammar books; Amharic curricula developers and text book writers should include all aspects of grammar knowledge of the target language-Amharic.*

## አህጽሮተ ጥናት

*ሰዋስው በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ለብዙ ሺህ ዓመታት ያህል ቁልፍ ቦታ ነበረው፡፡ ቋንቋን ማስተማር ማለት ሰዋስውን ከማስተማር ተለይቶ አይታይም ነበር፡፡ ዛሬም ቢሆን በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ሰዋስው ትልቅ ቦታ እየተሰጠው ነው፡፡ ከዚህ በመነሳት የዚህ ጥናት ዓላማ ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ የሚያስተምሩ መምህራን ያላቸውን የሰዋስው እውቀት እና ዋና ዋና ሰዋስዋዊ ስህተቶችን መፈተሽ ነበር፡፡ በዚህ መሰረት ናሙናዎች በጠቅላይ*

*የንሞና ስልት ተመርጠው መረጃዎችን በሰዋስው ፈተና ለመሰብሰብ ተችሏል፡፡ የሰዋስው ፈተናው 35 ጥያቄዎች ያሉትና በምርጫ መልክ የቀረበ ነው፡፡ በሰዋስው ፈተና የተሰበሰበውን መረጃ ደግሞ ነጠላ ናሙና ቲ-ቴስትን በመጠቀም ተተንትኗል፡፡ የተገኘው ውጤትም የመምህራን የሰዋስው እውቀት ዝቅተኛ (N=46፣t=-4.69)= 29.8፣P<0.05 መሆኑን ያሳያል፡፡ ሁለተኛውን መሰረታዊ ጥያቄ በተመለከተ ደግሞ መምህራን የሚዩባቸው ዋና ዋና ሰዋስዋዊ ስህተቶች መዋቅራዊ አቻዊነት፣ የሃሳብ ትስስር ስህተት፣ የመደብና የጊዜ፣ የጾታ እና የቁጥር ስህተቶች እንደቅደም ተከተላቸው ከአንደኛ እስከ አምስተኛ ደረጃ መያዛቸውን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ከዚህ በመነሳት ችግሩን ይቀርፋሉ የተባሉትን የመፍትሄ ሃሳቦች በማቅረብ ጥናቱን ለማጠናቀቅ ተችሏል፡፡ ይኸውም ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ የሚያስተምሩ መምህራን የሰዋስው እውቀታቸውንየተለያዩ የሰዋስው መፃህፍትን በማንበብ ቢያሻሽሉ፤ የመማሪያ መፅሀፍ አዘጋጆች የሰዋስው ትምህርቱን ሲያቀርቡ ሁሉንም ሰዋስዋዊ ስህተቶች ባካተተ መልኩ ማቅረብ ቢችሉ የመምህራንን የሰዋስው እውቀት ያሳድጋል ተብሎ ይታሰባል፡፡*

**ቁልፍ ቃላት፡-** ሰዋስው፣ የሰዋስው እውቀት፣ የሰዋስው ስህተት

## 1. መግቢያ

### 1.1 የጥናቱ ዳራ


ሰዋስው የቋንቋውን መምህር ለማሰልጠን፣ መማሪያ መፃህፍትን ለማዘጋጀትና የይዘቶችን ቅደምተከተል ለመወሰን ወዘተ አስፈላጊነቱ አከራካሪ አይደለም፡፡ የChomsky (1965) የቋንቋ ብቃት ንድፈሃሳብና ሁለንተናዊ ሰዋስው በሥነ-ልሳን ላይ የሚደረገውን ምርምር ባህሪና አቅጣጫ መሰረታዊ በሆነ መንገድ በመቀየር አፍላቂ ሰዋስው የሚባል አዲስ የሰዋስው መስክ እንዲመሰረት አደረገ፡፡ ይህም የሰዋስው ዓይነት ለሰው ልጆች ቋንቋ የጋራ የሆነውን ሁለንተናዊ ባህሪ የሚያጠና ነው፡፡ የChomsky (1965) አቋም የሥነ-ልሳን ምርምር ማተኮር ያለበት በቋንቋ ክህሎት (Language Performance) ላይ ሳይሆን በቋንቋ ብቃት (Language Competence) ላይ ነው፡፡

መዋቅራዊ ሥነ-ልሳን የሚያተኩረው ግን በንግግርና በፅሁፍ በሚቀርበው የቋንቋ ክህሎት ላይ ነው፡፡ Chomsky (1965) እንደሚለው የቋንቋ ብቃት ፍፁም ወይም ንፁህ የሰዋስው እውቀት ስለሆነ ውጫዊ በሆኑ ተላውጦዎች ተፅዕኖ አይደርስበትም፡፡ ማህበራዊ ተላውጦዎች ከሚባሉት ውስጥ ለምሳሌ የተግባቦቱ ዓላማ፣ በተናጋሪዎች መካከል ያለው ግንኙነት ወዘተ ከብቃት ጋር ግንኙነት የላቸውም፡፡ በተናጋሪው ክህሎት ላይ ግን ተፅዕኖ ሊያሳድሩ ይችላሉ፡፡

ለዚህም ነው Keck and Kim (2014) የቋንቋ ብቃት ከሰዋስው በላይ ነው የሚሉት፤ የChomsky የቋንቋ ብቃት ንድፈሃሳብ ግን በሰዋስው ላይ ብቻ የተወሰነ በመሆኑ የማህበራዊ ስምምነት እውቀት (Knowledge of Social Coventions) እና የተራክቦን ህግ (Rule of Interaction) አለማካተቱን ይገልፃሉ፡፡ የቾምስኪን የቋንቋ ብቃት ግንዛቤ በተመለከተ ጥያቄ የሚያቀርቡት Hymes (1972) ሲሆኑ ልጆች ከሰዋስው አንፃር ትክክለኛነት የተላበሱ ዓረፍተነገሮችን የማፍለቅ ችሎታ ብቻ ሳይሆን በአንድ የተወሰነ ሁኔታ ወይም አውድ ውስጥ የበለጠ ተስማሚ ወይም ተገቢ የሆነውን ቃል የመምረጥ ችሎታ ጭምር ያዳብራሉ፡፡

ከዚህ የምንረዳው የቋንቋ እውቀት ማለት የሰዋስው እውቀት ብቻ ሳይሆን የማህበራዊ ተራክቦ ጭምር ነው፡፡ እነዚህን ህጎች ህፃናት እንደሰዋስው ህጎች በግልፅ አይማሯቸውም፡፡ እውቅ የሆነ ትኩረት ባይሰጡም እነዚህን ህጎች እንዲከታተሉ ይማራሉ፡፡ እናም Hymes (1972) እንደሚሉት የቋንቋ ብቃት ከሰዋስው ብቃት በላይ በመሆኑ የቋንቋን ብቃት ለማጥናት አዲስ ፅንሰሃሳባዊ ማዕቀፍ (Framework) ያስፈልጋል፡፡ ይህም የተግባቦት ብቃት ንድፈሃሳብ ይባላል፡፡ በዚህ ንድፈሃሳብ መሰረት የማህበራዊ ስምምነት እውቀት የሰዋስው ህጎችን እውቀት ያህል አስፈላጊ ነው፡፡


ከተግባቦታዊ ብቃት አንፃር Bachman and Palmer (1996) ተግባቦታዊ የቋንቋ ችሎታ የሚል ሞዴል ያቀረቡ ሲሆን፣ በዚህ ሞዴል ብዙ ንዑስ የቋንቋ እውቀት ክፍሎችን በመለየት እንደሚከተለው በስእላዊ መግለጫ አቅርበዋቸዋል፡




ስእል 1፡-የቋንቋ እውቀት ክፍሎች

ከላይ እንደሚታየው ሞዴሉን በሁለት ዋናዋና ክፍሎች ይከፍሉታል፡፡ እነዚህም ክፍሎች የአደረጃጀት እውቀትና የቋንቋ አጠቃቀም እውቀት ናቸው፡፡ የአደረጃጀት እውቀት የሰዋስው እውቀትና የአሃድ እውቀት ተብሎ ይከፈላል፡፡ የቋንቋ አጠቃቀም እውቀት በተራው አገልግሎታዊና ማህበረ-ሥነልሳናዊ እውቀት ተብሎ ይከፈላል፡፡ በዚህ ሞዴል የቋንቋ አጠቃቀም እውቀት የሰዋስው እውቀት አካል ተደርጎ አልቀረበም፡፡ ነገርግን ሰዋስው የአደረጃጀት እውቀት (ሥነ-ድምፅ፣ሥነ-ምዕላድ፣ቃላትና ዓረፍተነገር ወይም አሃድ) በሚል ቀርቧል፡፡ ይህ የሰዋስው እውቀት ግንዛቤ Larsen-Freeman (2003) ሶስት ክፍሎች ካሉት Keck and Kim (2014) እንደገለፁት ደግሞ Purpura (2004) ከ Larsen-Freeman (2003) የሶስትዮሽ ሞዴል በመነሳት የራሳቸውን የሰዋስው እውቀት የተሰኘውን ሞዴል አቅርበዋል፡፡ ተመራማሪው ቅርፅና ፍችን የሰዋስዋዊ እውቀትሁለት ዋና ክፍሎች ናቸው ይሉና አጠቃቀምን (Use) ደግሞ ለብቻ ያቀርቡታል፡፡ በ Larsen-Freeman (2003) ግን ሶስቱም ክፍሎች (ቅርፅ፣ ፍችና አጠቃቀም) የሰዋስዋዊ እውቀት ክፍሎች እንደሆኑ ይጠቀሳሉ፡፡ ይህን የ Purpuraን የሰዋስው አተያይ የተለየ ነው፡፡ ምክንያቱም በLarsen-Freeman አጠቃቀም (Use/Pragmatics) የተሰኘው ሶስተኛው ክፍል የሰዋስው አካል ተደርጎ ነው የቀረበው:: በእርግጥ የLarsen-Freeman ሞዴል የተዘጋጀው ለምዘና ዓላማ ሳይሆን ሁለተኛ ቋንቋን ለማስተማር ነበር፡፡ በሌላ አባባል የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ግብ ተግባቦታዊ ብቃትን ማዳበር ከሆነ የሰዋስው ትምህርት ከቋንቋ አጠቃቀምጋርተሳስሮ መቅረብ አለበት፡፡ ይህም ተማሪዎች ሰዋስዋዊ ትክክለኛነታቸውን የጠበቁ ዓረፍተነገሮችን እንዴት እንደሚመሰርቱ ብቻ ሳይሆን በአንድ አውድ ውስጥ እንዴት መጠቀም እንዳለባቸውም ይረዳሉ::

የሰዋስው እውቀት ሞዴል እንደሚከተለው ያቀርባሉ::




ስእል 2፡-የሰዋስው እውቀት ሞዴል

በPurpura (2004) ሞዴል መሰረት ሰዋስዋዊ ቅርፅ ሲባል ሥርዓተ-ፅህፈት (Graphology)፣ ሥነ-ድምፅን፣ የድስኩር አላባውያንን ወይም አያያዥ ቃላትን የመሳሰሉትን ያካትታል፡፡ ሰዋስዋዊ ፍች ሲባል ደግሞ ሌጣ ፍች (Literal Meaning) ወይም መዝገበ ቃላዊ ፍችና እንዲተላለፍ የተፈለገው ፍች (Intended Meaning) የያዘ ነው፡፡ በሰዋስዋዊ ፍች ውስጥ ምንም እንኳን ሊተላለፍ የተፈለገው ፍች ከሰዋስውና ከአጠቃቀም (Pragmatic) አንፃር የተወሰነ መደራረብ ቢፈጥርም ሰዋስዋዊ ፍች የሚገለጸው ከቃላቱ፣ ከምዕላዱና ከአገባቡ አንፃር ነው፡፡ በሌላ በኩል የአጠቃቀም ፍች በቀዳሚነት የሚተረጎመው አንድ ሰው ለአውድ ካለው እውቀት አንፃር ነው፡፡ ይህ ጥናት የሚያተኩረው ሰዋስው ላይ በመሆኑ የLarsen-Freeman (2003) የሶስትዮሽ ሞዴል የተከተለ ነው፡፡ ምክንያቱም በዚህ ሞዴል አጠቃቀም የሰዋስው አካል ተደርጎ ነው የቀረበውና፡፡

Bygate (1994፣18) እንደሚሉት መምህራን ሰዋስውን ማወቃቸው ተግባቦትንና ሥርዓትን ለየብቻ ለይተው ትኩረት እንዲሰጡ ያስችላቸዋል፤ ተማሪዎች የሚገጥሟቸውን ሰዋስዋዊ ችግሮች መተንተን ይችላሉ፤ የተማሪዎችን የቋንቋ አጠቃቀም (ፅህፈት) ከሰዋስው አንፃር በልበ ሙሉነት በተለይም ትክክለኛነቱን፣ ተገቢነቱን (Appropriateness) እና ገላጭነቱን (Expressiveness) መገምገምና ለተማሪዎች በተለያየ ደረጃ ግልፅ የሆነ

የሰዋስው ትምህርት እንዴት ቀለል (Simplify) ተደርጎ መቅረብ እንዳለበት ለመረዳትና ለመተግበር ወዘተ. እንደሚያስችል ይገልፃሉ፡፡

ነገር ግን ምንም እንኳን ሰዋስው የቋንቋ ክሂሎችን ለማሻሻል አስተዋፅኦ ያለው መሆኑ ቢታወቅም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን በርካታ ፈተናዎች ተደቅነውበታል፡፡ ለአብነት በክረምቱ መርሃ ግብር ወደ ዩኒቨርሲቲያችን ትምህርታቸውን ለማሻሻል የሚመጡና የረጅም ጊዜ ቋንቋውን የማስተማር ልምድ ያላቸው መምህራን ሳይቀር "በሳል ፅህፈት" የተባለውን ኮርስ ሳስተምር በአማርኛ ቋንቋ ያላቸው የሰዋስው እውቀት አነስተኛ ነበር፡፡ በመፃፍ ክሂል ላይም በርካታ ሰዋስዋዊ ስህተቶችን እንደሚፈፅሙ ለማየት ችያለሁ፡፡ በተለይ የአማርኛ ቋንቋ አጠቃቀም ከጊዜ ወደ ጊዜ በተለያዩ ምክንያቶች ችግሮች ይስተዋሉበታል፡፡ ከምክንያቶቹ ውስጥ አንዱ የጥንቃቄ ጉድለትና ለስህተት ትኩረት ባለመስጠት መልመድ ነው (አምሳሉና ደምሴ ፣1982)፡፡አጥኚውም እነዚህ ችግሮች ከዚህ በፊት በነበረው የማስተማር ልምድ በመደበኛውም ሆነ በክረምቱ መርሃ ግብር በሚሰለጥኑ መምህራን ላይ በስፋት የሚስተዋሉ መሆናቸውን ለማየት ችሏል፡፡ ስለሆነም ከእነዚህ የፅሁፍ ቋንቋ ችግሮች ውስጥ አንዱ የሆነውን የመምህራንን የሰዋስው እውቀት እና የሚፈጽሟቸውን ዋና ዋና ሰዋስዋዊ ስህተቶችን ለይቶ ማጥናት፣ የመፍትሄ ሀሳቦችን መጠቆምና ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

### 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ሰዋስው በቋንቋ ትምህርትውስጥ ለብዙ ሺህ ዓመታት ያህል ቁልፍ ቦታ ነበረው፡፡ ቋንቋን ማስተማር ማለት ሰዋስውን ከማስተማር ተለይቶ አይታይም ነበር፡፡ ሰዋስውም እንደ ይዘት፣ ሥርዓተ ትምህርትንና የቋንቋ ማስተማሪያ መሳሪያዎችን ለማዘጋጀት እንደ ማደራጃ መርህ (Organizing Principles) ያገለግል ነበር፡፡ ቋንቋ ማለት የሰዋስው ህጎችን የያዘ በመሆኑ ተማሪዎች ቋንቋውን ለማወቅ እነዚህን ህጎች ማወቅ በቂ ነው ተብሎ ይታሰብ ነበር (Ellis ,2002፡ 145;Nassaji & Fotos,2011፡2)፡፡ Egyankosh(n.d)የተባሉ ፀሀፊ እንዳቀረቡት ግን ሰዋስው በቋንቋ ማስተማር ውስጥ ጉልህ ድርሻ አለው፡፡ ይሁን እንጅ "መኪና መንዳት ከፈለግህ የግድ የመኪናውን ውስጣዊ ክፍል፣ እያንዳንዱን ማወቅ የለብህም፤ሁሉንም ማወቅ ሳይጠበቅብህ መኪናህን መንዳት ትችላለህ" በማለት ግልፅ የሆነ ስለ ሰዋስው እውቀት ሳይኖረን መናገር ወይም መፃፍ እንደምንችል

ይገልፃሉ፡፡ ባየ (2000፣xxv) ደግሞ ከሹፍርና ስራ ጋር በማነፃፀር የቋንቋን ሥርዓትና አጠቃቀም ያወቀ ተማሪ ከተራ ሹፌር እንደሚለይና እንዲያውም እንደ መካኒክ ሹፌር እንደሚቆጠር ይገልፃሉ፡፡ ከላይ በተጠቀሱት ምሁራን ዘንድ በሰዋስው አስፈላጊነት ላይ የሚስማሙ ቢሆንም የትኩረት ልዩነት ያለ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ ለዚህም ነው Coleman & Klapper (2005፡8) "በቋንቋ ማስተማር ውስጥ የሰዋስው ትምህርት በጣም አከራካሪ ጉዳይ ነው" በማለት የሚገልፁት፡፡

ሰዋስው መምህራንን ጥሩ የቋንቋ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያስችላቸዋል፡፡ ይኸውም ጥሩ ተናጋሪ ፣ፀሀፊ፣ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል፡፡ ለዚህም ነው Nassaji and Fotos (2004፣ 137) "ሰዋስውን ማስተማር ፅህፈትን ከማስተማር ተለይቶ አይታይም፤ የመፃፍ ክሂልምቀጥተኛ የሆነ የሰዋስው ትምህርትን የያዘ ነው" በማለት የሚናገሩት፡፡ ከዚህ በተጨማሪ Brown (2000፣362) "ሰዋስው አያስፈልግም ብሎ የሚናገር፣ተግባቦት እንዲሳካ ሰዋስው ቀዳሚ መሆኑን የሚጠራጠር አንድም የለም" በማለት ሲገልፁ Nassaji and Fotos (2011፣1) እና Ellis (2006፣96) በበኩላቸው "ሰዋስው ለቋንቋ መሰረታዊ ነገር ነው፡፡ ያለ ሰዋስው ቋንቋ መኖር አይችልም፤ይሁን እንጅ በቋንቋ ማስተማር እንደ ሰዋስው አጨቃጫቂ የሆነ ነገር የለም፡፡ ክርክሩ ሰዋስውን ቀጥተኛ ወይስ ኢ-ቀጥተኛ በሆነ መንገድ ነው ማስተማር ያለብን በሚሉት ጉዳዮች ላይ ነው"ይላሉ፡፡

በቀደምት መንግስታት ጊዜ ለቋንቋው ይሰጠው የነበረው ትኩረት እጅግ ከፍተኛ ነበር፡፡ ይህን ሁኔታ ይትባረክ (2006) መምህር ፍስሃ ጽዮን (1983)ን ጠቅሰው እንዳቀረቡት በአፄ ገብረ መስቀል ዘመነ መንግስት ጊዜ (አክሱም) ፊደላትን አዛብቶ የፃፈ ተከሶ ይፈረድና ይቀጣ ነበር፡፡ በአፄ በካፋ (ጎንደር) ዘመነ መንግስት ጊዜም ፊደላትን አዛብቶ የፃፈ እጁ ይቆረጥ ነበር ይላሉ፡፡ የሚገርመው ግን በአሁኑ ሰዓት ለአማርኛ ቋንቋ የሚሰጠው ትኩረት አናሳ መሆኑ ብቻ ሳይሆን በባለቤትነት የሚያስብለት አካል አለመኖሩ ነው፡፡ በዚህም የተነሳ ያለው እንዳወቀ በኩር (መጋቢት 1991 ዓ/ም) ን በመጥቀስ "አማርኛ ወገን የሌለው ቋንቋ ነው" ይሉታል፡፡

መምህራን ትክክለኛውን ሰዋስዋዊ ቅርፅና አገልግሎት ካላወቁ በክፍል ውስጥ የሚያስፈልገውን መደበኛ የፅህፈት ቋንቋ መጠቀም አይችሉም፡፡ እናም አንድ የህንፃ ባለሙያ ንድፉን (Blue Print) ተጠቅሞ ማራኪና ቆንጆ ህንፃ እንደሚገነባ ሁሉ

አንድ ፀሀፊም ቃላትን ተጠቅሞ በጥሩ ሁኔታ የተዘጋጀ ፅሁፍ መፍጠር አለበት፡፡ መሀንዲሱ የፊዚክስን ህግ መረዳት እንዳለበት ሁሉ ፀሀፊውም የቋንቋውን ህግ እና የቃላትን ባህሪ መረዳት ይኖርበታል (Cook &et al. ፣2010)፡፡

አንድ ሰውም አንድን ቋንቋ ያውቃል የሚባለው ቋንቋውን እንደ ማህበራዊ አውዱ ሲጠቀምበት ወይም የቋንቋውን ሰዋስዋዊ ህግና የተናጋሪውን ባህል ጠብቆ ቋንቋውን አገልግሎት ላይ ካዋለ ነው፡፡ ይህም አንድ ፀሀፊ ወይም ተናጋሪ ከቋንቋው ሰዋስዋዊ ባህርያት በተጨማሪ ማህበራዊ የሆነውን የቋንቋ አጠቃቀም ለይቶ ማወቅ እንዳለበት የሚያመለክት ነው፡፡ ማለትም አንድን ቋንቋ የት፣ እንዴት፣ መቼ፣ ለማን ወዘተ ነው መጠቀም ያለብኝ የሚለውን ማወቅ ይኖርበታል፡፡ የፅህፈት ስራም በአንፃራዊነት ከንግግር የበለጠ ልዩ ጥንቃቄን የሚጠይቅበት አንዱ ምክንያት በፅህፈት ጊዜ ምልክታዊ መግባቢያዎች መጠቀም ስለማንችል ነው፡፡

Bush (2006፣77) በሚቺጋን ዩኒቨርሲቲ ባካሄዱት ጥናት ያገኙት ውጤት እንደሚያሳየው የመጻፍ ክሒል እንዲዳብር ከተፈለገ የሰዋስው እውቀትን ማሳደግ ተገቢ ነው፡፡ ምክንያቱም ሰዋስው የመጻፍ ክሒል ተፈጥሯዊ አካል በመሆኑ ተማሪዎች ወይም መምህራን ሰዋስዋዊ እውቀት ከሌላቸው ወይም እውቀታቸው ዝቅተኛ ከሆነ በጽሑፍ ማስተላለፍ የሚፈልጉትን ሀሳብ አንባቢዎች ሊረዱት በሚችሉት መንገድ መግለፅ አይችሉም፡፡

የመምህራን የመጻፍ ክሒል ችግር በተለያዩ ምክንያቶች ሊከሰት ይችላል፡፡ ከምክንያቶቹ ውስጥ ትልቁን ድርሻ የሚይዘው የመምህራን የሰዋስው እውቀት ማነስ እንደሆነ የተለያዩ ጥናቶች ያመለክታሉ፡፡ Trong (2012) በቬትናም ሆቺሚንህ ከተማ ፋይናንስ ማርኬቲንግ ዩኒቨርሲቲ ከሰራው ሙከራዊ ጥናት ያገኘውን ውጤት መሰረት አድርጎ እንደገለፀው ለመምህራን የመጻፍ ክሒል ችግር ዋናው ምክንያት የመምህራን የሰዋስው እውቀት ማነስ ነው፡፡ Trong (2012) በጥናቱ ውጤት እንዳረጋገጠው መምህራን ሲጽፉ ከሚፈጽሟቸው ስህተቶች ውስጥ 75% የሚሆነው የሰዋስው ስህተት ነው፡፡

ሌላው የመምህራንን የሰዋስው እውቀት ኢ-ቀጥተኛ በሆነ መንገድ የሚፈትሽ ጥናት በፋንታየ (2011ዓ/ም) የተከናወነ ጥናት ሲሆን ይዞት የተነሳው ዓቢይ አላማ በአማራ ክልል፣ በምዕራብ ጎጃም ዞን፣ በሰከላ ወረዳ፣ ግሽ ዓባይ ከተማ እና ዙሪያ በሚገኙ አምስት አንደኛ ደረጃ እና ሙሉ ሳይክል ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ

የአማርኛ ቋንቋ መምህራንን የመፃፍክሂል ችሎታ ማጥናት ነው:: ጥናቱንም ከግብ ለማድረስ አጥኝዋ ቅይጥ የምርምር ንድፍ (mixed Research Design) ተጠቅማለች:: የመረጃ ምንጮች ፈተና እና የጽሁፍ መጠይቆች ናቸው:: መረጃዎችም በቁጥር መረጃ ትንተናና በገላጭ ንድፍ አቀራረብ ትንተና ተደርጎባቸዋል:: የጥናቱ ግኝትም ከግማሽ በላይ የሚሆኑት መምህራን የጻፏቸው አንቀጾች ሀሳባቸው በበቂ ሁኔታ ያልተገለጸ፣ በአግባቡ ያልተደራጁ እና የቋንቋ አጠቃቀማቸውም የተለያየ ችግር ያለበት መሆኑ ጥናቱ ያመላክታል:: በመሆኑም የጥናቱ ግኝትን መሰረት በማድረግ ሁሉም መምህራን ያላቸውን የመፃፍ ክሂል ክፍተት እንዲያጠቡ ስለ ክሂሉ የሚያግዙ የተለያዩ አጋዥ መጽሀፎችን ቢያነቡ፤ ከተመሳሳይ የስራ ባልደረቦቻቸው ጋር ልምድ ቢለዋወጡ፤ የሚመለከታቸው አካላት ለመምህራን አላማውን የጽሀፈት ክሂል ማጎልበት ያደረገ የስራ ላይ ስልጠና እንዲሰጡ ወዘተ ቢያደርጉ ለመምህራን የመፃፍክሂል ማደግ አስተዋጽኦ ያደርጋል የሚሉ አስተያየቶችን ሰጥታለች::

ይህን ጥናት ከፋንታየ ጥናት ጋር የሚያመሳስላቸው ጉዳይ የመፃፍ ክሂል ችሎታ አንዱ መለኪያ የሰዋስው ችሎታ በመሆኑ ሁለቱም ጥናቶች የሰዋስውን ችሎታ የጋራ ባህሪ አድርገው መጠቀማቸው ነው:: ልዩነታቸው ግን ይህ ጥናት የሚያተኩረው በመምህራን የሰዋስው ችሎታ እና በሚፈጽሟቸው ዋና ዋና ሰዋስዋዊ ስህተቶች ላይ ብቻ ሲሆን የፈንታዬ (2011) ጥናት ግን በመፃፍ ክሂል ችሎታ ላይ የሚያተኩር ነው:: ሌላው ፈንታዬ መረጃዎችን ለመተንተን ቅይጥ የምርምር ንድፍ (mixed Research Design) ስትጠቀም በዚህ ጥናት ግን ነጠላ ናሙና ቲ- ቴስት እና የስህተት ቆጠራ ዘዴ ተግባራዊ ሆኗል::

ከላይ የተጠቀሱት ጥናቶች እንደሚያመለክቱት የመምህራን የመጻፍ ክሒል በጣም ዝቅተኛ ነው:: ይህም ከሆነባቸው ምክንያቶች ውስጥ ዋናው የሰዋስው እውቀታቸው ዝቅተኛ መሆን ነው:: ስለዚህ የመጻፍ ክሒል ችሎታቸው እንዲያድግ ከተፈለገ የሰዋስው እውቀት ማደግ አለበት:: በመሆኑም ይህ የዳሰሳ ጥናት የታሰበውን ዓላማ ለማሳካት የሚከተሉትን መሰረታዊ ጥያቄዎች ይመልሳል::

1ኛ. ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ የሚያስተምሩ መምህራን ያላቸው የሰዋስው እውቀት ምን ያህል ነው?

2ኛ. ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ የሚያስተምሩ መምህራን ከፍተኛውን ሰዋስዋዊ ስህተት የሚሰሩት ምን ምን ላይ ነው?

### 1.3. የጥናቱ ዓላማዎች

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሰዋስው እውቀትና የሚታዩባቸው ዋና ዋና ሰዋስዋዊ ስህተቶች ፍተሻ የሚል ሲሆን፣ ዝርዝር ዓላማዎቹም የሚከተሉት ናቸው፤

1ኛ. ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ የሚያስተምሩ መምህራን ያላቸው የሰዋስው እውቀት ምን ያህል እንደሆነመመርመር፤

2ኛ. ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ የሚያስተምሩ መምህራን ከፍተኛውን ሰዋስዋዊ ስህተት የሚሰሩት ምን ምን ላይ እንደሆነ መፈተሽ፤

### 1.4. የጥናቱ አስፈላጊነት

የሰዋስው እውቀት በአንድ ቀን የሚዳብር ስላልሆነ፣ በችግሮች ዙሪያ በየጊዜው መወያየት፣ መነጋገር፣ ምርምር ማካሄድ፣ አጫጭር ሴሚናሮችን ማቅረብ ወዘተ. ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም ይህ ጥናት ከተጠናቀቀ በኋላ የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል፡፡

1ኛ. ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ ለሚያስተምሩ መምህራን ስለ ሰዋስው ያላቸውን እውቀት ይጠቁማል፡፡

2ኛ. ለመርሃ ትምህርት ቀራጮች፣ ለመፅሃፍ አዘጋጆች፣ ባጠቃላይ ለትምህርት ባለሙያዎች ስነትምህርታዊ እገዛ ያደርጋል፡፡ ይኸውም ከተለያዩ ክሂሎች ጋር ሰዋስዋዊ መልመጃዎች እንዴት ተቀናጅተው እንደቀረቡና ምን ያህል ትኩረት እንደተሰጣቸው ራሳቸውን እንዲፈትሹ ያግዛል፡፡

3ኛ. ከዚህ ጥናት ርዕሰ ጉዳይ ጋር በተያያዘ፣ በመስኩ ለሚደረጉ ሌሎች ምርምሮች መነሻ በመሆን ያገለግላል፡፡

### 1.5. የጥናቱ ገደብ

ይህ ጥናት ዋና ዓላማ አድርጎ የተነሳው ከ9ኛ እስከ12ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ የሚያስተምሩ መምህራንን የሰዋስው እውቀት መመርመር ነው፡፡ ትኩረቱም በአምስት መሰናዶ ትምህርትቤቶች ውስጥ አማርኛን ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል እንደአፍ መፍቻ ቋንቋ በሚያስተምሩ መምህራን ላይ ብቻ ተወስኗል፡፡ ከይዘት አንፃርም ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል የሚገኙ መምህራንን የሰዋስው እውቀት እና የሚታዩባቸው ዋናዋና ሰዋስዋዊ ስህተቶችን መመርመር ላይ ብቻ ያተኩራል፡፡

### 1.6 የጥናቱ ውሱንነት

ይህ ጥናት የተከናወነው በደብረማርቆስ ከተማ ሥር በሚገኙ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ ነው፡፡ ትምህርት ቤቶቹ መረጃ ለመሰብሰብ ካላቸው የቦታ፣ የገንዘብ፣ የጉልበትና የጊዜ ምቹነት አንፃር በአመቺ የንሞና ዘዴ ተመርጠዋል፡፡ በመሆኑም የተገኘው ውጤት ሌሎችን ትምህርት ቤቶች ሊያጠቃልል ወይም ሊወክል አይችልም፡፡

**1.7. የቁልፍ ቃላት አጠቃቀም፡፡**

**ሰዋስው፡-** በዚህ ጥናት ሰዋስው ሲባል ቅርፅ (Form)፣ ፍች (Meaning) እና አገልግሎት (Use) የሚሉትን ክፍሎች አጣምሮ የያዘ ነው፡፡

**የሰዋስው እውቀት፡-** ሰዋስዋዊ ተቀባይነት እና ማህበራዊ ተቀባይነት ያላቸውን ዓ/ነገሮች መጠቀም መቻል ማለት ነው፡፡

**ሰዋስዋዊ ስህተት፡-**በዚህ ጥናት ሰዋስዋዊ ስህተት ሲባል የቁጥር፣ የጾታ፣ የመደብ፣ የጊዜ፣ መዋቅራዊ አቻዊነት እና የሃሳብ ትስስር የተሰኙ ስህተቶችን የያዘ ነው፡፡

**2. የአጠናን ዘዴ**

ይህ ጥናት የተከተለው የፍልስፍና ዓለም አተያይ የፍፁማውያን አተያይ (The positivist Worldview) ነው፡፡ በዚህ የፍልስፍና አተያይ መሰረት አንድ ምርምር ጠንካራና ሳይንሳዊ ሥርዓትን የሚከተል፣ ስታቲስቲክስና የስታቲስቲክስ ቋንቋን የሚጠቀም ነው፡፡ ተጨባጭ እውነታ ላይ ለመድረስ የታወቀ (Standardized) ሂደትን ይከተላል፡፡ በአጠቃላይነትና በዓለማቀፋዊ ህግ (Generalizability and Universal Law) ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ የምርምሩ ዓይነት መጠናዊ ስለሆነ በንድፈሃሳባዊ ማዕቀፍ (Theoretical Frame work) ላይ የሚመሰረትና አካሄዱም ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር በመሆኑ ቀናሽ (Reductionistic) የተባለውን መርህ የሚከተል ነው፡፡ ይህ ጥናት ከ 9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ የሚያስተምሩ መምህራንን የሰዋስው ችሎታ ወይም እውቀትና የሚታዩባቸውን ዋናዋና ስህተቶች ይፈትሻል፡፡ ስለሆነም ምርምሩ ቅኝታዊ የጥናት ንድፍን የተከተለ ነው፡፡ ከዚህ በመነሳት ይህ ጥናት በመጠናዊ ዘዴ (Quantitative Method) ላይ የተመሰረተ ነው፡፡

2.1. **የጥናቱ ተሳታፊዎች**

ይህ ጥናት በደብረማርቆስ ከተማ በሚገኙ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ የተካሄደ ነው፡፡ ይኸውም ደብረማርቆስ ከተማ ከቅርበት አንፃር በአመቺ የንሞና ዘዴ ተመርጧል፡፡ በደብረማርቆስ ከተማ ደግሞ 5 ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ማለትም ኢትዮ-ጃፓን፣ መንቆረር፣ ንጉስ ተ/ሃይማኖት፣ ደብረማርቆስና ጎዛምን ይገኛሉ፡፡ እነዚህ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት

ቤቶች መረጃ ለመሰብሰብ ካላቸው ቅርበት አንፃር ሁሉም በአመቺ የንሞና ዘዴ ተመርጠዋል፡፡ በመቀጠልም በእነዚህ ትምህርትቤቶች ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ የሚያስተምሩ 46 መምህራን በጠቅላይ የንሞና ስልት ተመርጠው የጥናቱ ተሳታፊ ሆነዋል፡፡ ጠቅላይ የንሞና ስልትየተመረጠበት ምክንያት በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚገኙ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ቁጥራቸው አነስተኛ ስለሆነ ነው፡፡

## 2.2. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

ለዚህ ጥናት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ በመሆን ያገለገለው የአማርኛ ቋንቋ የሰዋስው ፈተናነው፡፡ የሰዋስው ፈተናው የተሰጠው ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ በማስተማር ላይ የሚገኙ መምህራን በየደረጃቸው ማወቅ የሚገባቸውን የሰዋስው እውቀትና የሚታዩባቸውን ዋና ዋና ሰዋስዋዊ ስህተቶች በተመለከተ ያሉበትን ደረጃ ለመፈተሽ የሚያስችል ሲሆን የሚከተሉትን ነጥቦች ታሳቢ በማድረግ ተዘጋጅቷል፡፡

መምህራን ከዚህ በፊት በዩኒቨርሲቲ ደረጃ የተማሯቸውን የሰዋስው ኮርሶችና በመጀመሪያና በሁለተኛ ድግሪ የተመረቁመምህራን ማወቅ የሚገባቸውን ይዘቶች ታሳቢ በማድረግ ተዘጋጅቷል፡፡ ይኸውም የተዘጋጀው የሰዋስው ፈተና በምርጫ መልክ የቀረበ ሲሆን የቁጥር፣ የፆታ፣ የመደብ፣ የጊዜ፣ የመዋቅራዊ አቻዊነትና የሃሳብ ትስስር ችግር ያሉባቸው 35 ዓ/ነገሮች እንዲዘጋጁ ከተደረገ በኋላ ከ70% እንዲታረም ተደርጓል፡፡

## 2.3. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች አስተማማኝነትና ትክክለኛነት

Cohen (2000) እንደሚሉት አስተማማኝነትንና ትክክለኛነትን የሚቀንሱ ነገሮችን ሙሉ በሙሉ ማጥፋት አይቻልም፡፡ ከዚህ በመነሳት የአማርኛ ሰዋስው ጥያቄዎችን አስተማማኝነት በተመለከተ ከአምስቱ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤቶች ውስጥ የተገኘው መረጃም በ'እኩል ክፋይ ዘዴ' ተለክቶ የፈተናው አስተማማኝነት 0.675 ሆኗል፡፡ ይህም ሲጠጋጋ 0.7 በመሆኑ ከአምስቱ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤቶች ከሚገኙ መምህራን የተገኘው መረጃ አስተማማኝነት ያለው መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ የሰዋስው ፈተናውን የይዘት ትክክለኛነት በተመለከተ ደግሞ Cohen (2000)፣ Mujis (2004) እና Weir (1990) እንደሚሉት፣ የፈተናውን ይዘት በባለሙያዎች በማስገምገም ሁሉም ጥያቄዎች ወካይና ጠቃሚ መሆናቸው ተፈትሸዋል፡፡

## 2.4. የመረጃ መተንተኛ ስልቶች

በዚህ ጥናት የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስው ፈተና በመጠናዊ የመረጃ መተንተኛ ዘዴ ተተንትኗል፡፡ ይኸውም የመምህራን የሰዋስው እውቀት በነጠላ ናሙና ቲ- ቴስት ተተንትኗል፡፡ ሁለተኛውን መሰረታዊ ጥያቄ በተመለከተ ደግሞ መምህራን የሚታዩባቸው ሰዋስዋዊ ስህተቶች ማለትም የቁጥር፣የፆታ፣የጊዜ፣ የመደብ፣ የመዋቅራዊ አቻዊነትና የሃሳብ ትስስር ችግር ያሉባቸውን ዓረፍተ ነገሮች ድግግሞሻቸውን በቁጥርና በፐርሰንት በማስቀመጥ ለመተንተን ተችሏል፡፡

## 2.5. ሥነ-ምግባራዊ ሁኔታዎች

የጥናቱ ተሳታፊዎች ለምርምሩ የሚያስፈልጉ መረጃዎችን በነፃነት መስጠት እንዲችሉ የምርምር ሥነ-ምግባር መከበር አስፈላጊ ጉዳይ ነው፡፡ በዚህ መሰረት አጥኚው ጥናቱን ለማካሄድ በየደረጃው ከሚገኙ ባለድርሻ አካላት የትብብር ደብዳቤ ከማፃፍ ጀምሮ ከመረጃ ሰጭ አካላት (መምህራን) ጋር ስለ ምርምሩ ምንነትና ዓላማ ውይይት በማድረግ በምርምር ስራው በቅንነት እንዲሳተፉና መረጃ የመስጠት ሂደቱም በፍላጎት ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ተደርጓል፡፡ በዚህ ጊዜ ለምርምሩ የሚሰጡት መረጃ ከጥናቱ ዓላማ ውጭ እንደማይውልና የመረጃ ሰጭዎች ማንነትም ለማንም እንደማይገለፅ ተነግሯቸዋል፡፡

# 3.የመረጃ ትንተናና የውጤት ማብራሪያ

## 3.1 የመረጃ ትንተና

የዚህ ጥናት የመጀመሪያ ዓላማ ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ የሚያስተምሩ መምህራንን የሰዋስው እውቀት መፈተሽ ነው፡፡ በመሆኑም በፈተና የተሰበሰበው መረጃ በነጠላ ናሙና ቲ- ቴስት በሰንጠረዥ 3.1 እንደሚከተለው ተተንትኖ ቀርቧል፡፡

ሰንጠረዥ- 3.1 የመምህራን የሰዋስው እውቀት መለኪያ ፈተና ውጤት

| | **የናሙና ብዛት** | **የነፃነት ደረጃ** | **አማካይ** | **የሚጠበቅ አማካይ** | **መደበኛ ልይይት** | **የቲ ዋጋ** | **ጉልህነት** |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **የሰዋስው ፈተና** | 46 | 45 | 29.8 | 35 | 7.58 | -4.69 | 0.000 |

ከሰንጠረዥ3.1 እንደምንመለከተው የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሰዋስው እውቀት አማካይ ውጤት (29.8) ከሚጠበቀው አማካይ ውጤት (35) በታች ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይኸውም የመምህራን አማካይ የሰዋስው እውቀት ከሚጠበቀው አማካይ ውጤት በ5.2 ያነሰ ሲሆን ጉልህ ልዩነት ያለው (P=0.000) ሆኖ ተገኝቷል፡፡

የዚህ ጥናት ሁለተኛው ዓላማ ደግሞ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በአብዛኛው

የሚታዩባቸው ዋናዋና ሰዋስዋዊ ስህተቶች ምን ምን ናቸው የሚል ነበር። በዚህም የተገኘው መረጃ በሰንጠረዥ 3.2 እንደሚከተለው ተተንትኖቀርቧል።

ሰንጠረዥ-3.2 የመምህራን ሰዋስዋዊ ስህተቶች ዓይነትና ብዛት

| | **የስህተት ዓይነት** | **ድግግሞሽ** | **ፐርሰንት** | **ትክክለኛ ፐርሰንት** | **አጠቃላይ ድምር** |
|---|---|---|---|---|---|
| | የቁጥር | 5 | 10.2 | 10.6 | 10.6 |
| | የጾታ | 6 | 12.2 | 12.8 | 23.4 |
| | የመደብና የጊዜ | 7 | 14.3 | 14.9 | 38.3 |
| | መዋቅራዊ አቻዊነት | 19 | 38.8 | 40.4 | 78.7 |
| | የሃሳብ ትስስር | 10 | 20.4 | 21.3 | 100.00 |
| **ድምር** | | 47 | 95.9 | 100.0 | ----- |
| **የተዘለለ** | | 2 | 4.1 | ---- | ---- |
| **አጠቃላይ ድምር** | | 49 | 100 | ----- | ----- |

ከሰንጠረዥ- 3.2 ላይ እንደምንመለከተው ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ የሚያስተምሩ መምህራን በአንደኛ ደረጃ የሚታይባቸው ሰዋስዋዊ ስህተት መዋቅራዊ አቻዊነት (38.8%)ሲሆን በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ የሃሳብ ትስስር(20.4%) ነው። የመደብና የጊዜ(14.3%)፣ የጾታ(12.2%) እና የቁጥር (10.2 %) ስህተቶችም እንደቅደም ተከተላቸው ከ3ኛ እስከ 5ኛ ደረጃ የያዙ መሆናቸውን የተገኘው መረጃ ያመለክታል።

### 3.2. የውጤት ማብራሪያ

ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ የሚያስተምሩ መምህራን የሰዋስው እውቀት(29.8) ከሚጠበቀው አማካይ ውጤት(35) በታች ሆኖ በመገኘቱ ዝቅተኛ (P=0.000) ነው ማለት ይቻላል። ይህም አሳምነው (2015) መምህራን የሰዋስው ትምህርቱን በአውድ አስደግፈው እንደማያቀርቡ ከደረሰበት ውጤት ጋር ተደጋጋፊ ሆኖ ተገኝቷል። እንደዚሁም ኑርአይኔ (2015) መምህራን ተግባቦታዊ ሰዋስውን የተመለከተ ይህ ነው የሚባል እውቀት እንደሌላቸው ማረጋገጥ ተችሏል ብለው ከደረሱበት ውጤት ጋር ተመሳሳይ ሆኖ ተገኝቷል።ከዚህ በተጨማሪ ፋንታየ በ2011 ዓ/ም ከግማሽ በላይ የሚሆኑት መምህራን የጻፏቸው አንቀጾች ሀሳባቸው በበቂ ሁኔታ ያልተገለጸ፣ በአግባቡ ያልተደራጁ እና የቋንቋ አጠቃቀማቸውም

የተለያየ ችግር ያለበት መሆኑን ከጠቆሙት ጥናት ጋር ተደጋጋፊ ሆኖ ተገኝቷል።

## 4. ማጠቃለያና አስተያየት

### 4.1. ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ የሚያስተምሩ መምህራን ያላቸውን የሰዋስው እውቀት ምን ያህል እንደሆነ መፈተሽ እና የሚታዩ ዋና ዋና የሚባሉ የሰዋስው ስህተቶችን መለየት ነው። ዝርዝር ዓላማዎቹ ደግሞ፡-

1. ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ የሚያስተምሩመምህራን የሰዋስው እውቀት ምን ያህል እንደሆነ መገምገም።
2. ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ የሚያስተምሩ መምህራን የሚታዩባቸው ዋና ዋና የሰዋስው ስህተቶች ምን ምን እንደሆኑ መለየት ናቸው።

በዚህ መሰረት እነዚህን ዝርዝር ዓላማዎች ለመመለስ በደብረማርቆስ ከተማ የሚገኙ አምስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በአመቺ የንሞና ስልት ተመርጠዋል። በእነዚህ ትምህርት ቤቶች አማርኛ ቋንቋን ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል የሚያስተምሩ 46 መምህራንም በጠቅላይ የንሞና ዘዴ ተመርጠዋል። በመቀጠል የመምህራንን የዋስው እውቀት ለመፈተሽ የሚያስችል 35 ጥያቄዎች ያሉት የሰዋስው ፈተና እንዲዘጋጅ ተደረገ፡፡ የተሰበሰበው የሰዋስው ፈተናም በነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ተተንትኖ የተገኘው ውጤት እንደሚያሳየው መምህራን ያላቸው የሰዋስው እውቀት ዝቅተኛ እንደሆነ ለመረዳት ተችሏል። ሌላው ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ የሚያስተምሩ መምህራን የሚታዩባቸው ዋና ዋና የሰዋስው ስህተቶች በተመለከተም በመጀመሪያ ደረጃ መዋቅራዊ አቻዊነት ሲሆን፣ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ የሃሳብ ትስስር እንደሆኑ ለማረጋገጥ ተችሏል። የመደብና የጊዜ የጾታና የቁጥር ስህተቶችም እንደቅደም ተከተላቸው ከ3ኛ እስከ 5ኛ ደረጃ የያዙ መሆናቸውን የተገኘው መረጃ ይጠቁማል።

### 4.2. የመፍትሄሀሳብ

በዚህ ጥናት የተደረሰባቸውን ውጤቶችና በማጠቃለያው ክፍል ላይ የተገለፁትን ችግሮች ለማስወገድ ይረዳሉ ተብለው የታመነባቸው የመፍትሄ ሀሳቦች እንደሚከተለው ቀርበዋል።

- ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ የሚያስተምሩ መምህራን የሰዋስው እውቀታቸውን የተለያዩ የሰዋስው መፃህፍትን በማንበብ ቢያሻሽሉ፤
- በዩኒቨርሲቲ ደረጃ አማርኛ ቋንቋን በተለይም የአማርኛ ሰዋስውን

የሚያስተምሩ መምህራን ሰዋስዋዊ ስህተቶችን በተመለከተ ትኩረት ሰጥተው ቢያስተምሩ፡፡

- የመማሪያ መፅሀፍ አዘጋጆች የሰዋስው ትምህርቱን ሲያቀርቡ ስለተለያዩ ሰዋስዋዊ ስህተቶች ምንነት ማብራሪያ ከምሳሌ ጋር ማቅረብ ቢችሉ የመምህራንን የሰዋስው እውቀት በማሳደግ የሚታዩባቸውን ዋናዋና ሰዋስዋዊ ስህተቶች ለመቀነስ ያስችላል ተብሎ ይታሰባል፡፡

**ዋቢ ጽሑፎች**


ባየ ይማም፡፡ (1987)፡፡ *የአማርኛ ሰዋስው፡፡* አዲስ አበባ፣ ት.መ.ማ.ማ.ድ፡፡

ባየይማም፡፡ (2000)፡፡ *የአማርኛ ሰዋስው (የተሻሻለ)፡፡* አዲስአበባ፣ ት.መ.ማ.ማ.ድ

ያለውእንዳወቀሙሉ፡፡ (1998)፡፡ *የምርምር መሰረታዊ መርሆዎችና አተገባበር (ሁለተኛ እትም)*፡፡ ባህርዳር፣ አብክመ ትምህርት ቢሮ፡፡

ይትባረክ ገሠሠ ፡፡(2006)፡፡ *በኪነ ጽሀፌት ጊዜ የፊደላት አቀማመጥ፡፡* አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፡፡

አሳምነው ቦጋለ ፡፡ (2015)፡፡ ‹ የተግባቦታዊ ሰዋስው ትምህርት የክፍል ውስጥ አቀራረብ ፍተሻ፡- በ9ኛ ክፍል ተተኳሪነት፡፡ ያልታተመ የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናት፣ ኮተቤ የትምህርት ዩኒቨርሲቲ፡፡

ኑርአይኔ መሐመድ ፡፡ (2015) ፡፡ ‹‹ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስለ ተግባቦታዊ ሰዋስው የክፍል ውስጥ አተገባበር ፍተሻ በትግራይ ክልል ቃፍታ ሑመራ ወረዳ ቃፍታ 2ኛ እና መሰናዶ ትምህርት ቤት፣ 10ኛ ክፍል ተተኳሪነት፡፡” ያልታተመ የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናት፣ አክሱም ዩኒቨርሲቲ፡፡

Brown, D. (2000). *Principles of Language Learning and Teaching (4th Ed.).* California: Longman.

Bush , Jonathan (2006) “ Grammar intertwind through the Writing Process : An ‘inch wide and amile deep’” Western Michigan University, Kalamazoo: V.5,N.1,pp.77-101.

Bygate, M., Tonkyn, A., & Williams, E. (1994). *Grammar and the Language Teacher.* London: Prentice-Hall.

Byrne, D, (1988) teaching writing skills. London: longman group UK limited

Chomsky, N. (1965) Syntactic Structures. The Hague: Mounton Random House.

Cohen, L., Manion, L., & Morrison, K. (2000). *Research Methods in Education (5th Ed.).* London & New York: Routledge Falmer.

Coleman, J.A., & Klapper, J. (2005).*Effective Learning and Teaching in Modern Languages.* London & New York: Routledge.

Cook, H. (2010). *Academic Language/Literacy Strategies for Adolescents A "How To"*

*Manual for Educators*. New York & London: Routledge.

Cook Hirai, Debra L. and et al.(2010). *Academic Language /Literacy Strategies for Adolescents A "How To" Manual for Educators*. New York& London: Routledge.

Creswell, J.W. (2012). *Educational Research: Planning, Conducting and Evaluating Qualitative and Quantitative Research*. Boston. Pearson Education Inc. Egyankosh (n.d.) "Current Trends in Teaching Grammar"

Ellis, R. (2002). " Grammar Teaching Practice or Consciousness-Raising?" In Richards, J.C. & Renandya,Willy, A. (Eds.), *Methodology in Language Teaching: An Anthology of Current Practice,* (pp. 167-175). Cambridge: Cambridge University Press.

Ellis, R. (2006). " Current Issues in the Teaching of Grammar: An SLA Perspective." *TESOL QUARTERLY Vol.40, No.1.NewZealand*: University of Auckland.

Hyland, K. (2003). *Second Language Writing.* Hong Kong: Cambridge University Press.

Hymes, D. (1972) On Communicative Competence. In Pride, J.B. and Holmes, J. (eds.), Sociolinguistics. PP. 269-293. Harmondsworth, England: Penguin Books.

Keck, Casey and Kim, Youjin (2014) Pedagogical Grammar. Philadelphia: John Benjamins Publishing Company.

Larsen-Freeman,Diane (2003*).Techniques and Principles in Language Teaching (2nd ed.)*. Oxford: OUP.

Lea, M.R. and Street, B.V. (1998). Student Writing in Higher Education: an academic literacies approach. *Studies in Higher Education,* 23(2), 157-172.

Muijs, D. (2004). *Doing Quantitative Research in Education with SPSS.* London: Sage Publications.

Nassaji, H., & Fotos, S. (2011). " Current Developments in Research on the Teaching of Grammar." *Annual Review of Applied Linguistics, 24* , 126-145.

Purpura, James E (2004).*Assessing Grammar.* Cambridge: Cambridge University Press.

Richards J.C. (1974). *Error analysis perspectives on second language acquisition*. London and New York: Longman Group Ltd. Seed house, P (1997). Combing form and meaning: ELT Journal 51/4, 336-44.

Trong L. Tuan (2012) "Teaching Writing through Reading Integration" Finland: Journal of Language Teaching and Research. Vol.3, No.3, PP. 489-499.

Weir, C. (1990). *Communicative Language Testing.* London: Prentice-Hall International (UK) Ltd.